የ **2015** ዓ.ም የ **9** ወራት እቅድ አፈፃፀም መከታተያ ቼክሊስት

የሱፐርቪዥን ክላስተሮች **9** ወር ሪፖርቱ እነዚህን ነጥቦች እንዲያካትት ድጋፍ ይሰጥበት

የትኩረት መስክ **1**፡- ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት

ግብ **1**፡- ፍትሃዊ የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነትን ማሳደግ፣

- የትምህርት ጥቅል ቅበላ እንዲሻሻል የተደረገ ድጋፍ ክትትል (ከቅድመ 1 ኛ እስከ 2 ኛ ደረጃ)
- የትምህርት ንጥር ቅበላ እንዲሻሻል የተደረገ ድጋፍ ክትትል (ከቅድመ 1 ኛ እስከ 2 ኛ ደረጃ)
- የትምህርት ጥቅል ተሣትፎ እንዲሻሻል የተደረገ ድጋፍ ክትትል (ከቅድመ 1 ኛ እስከ 2 ኛ ደረጃ)
- የትምህርት ንጥር ተሣትፎ እንዲሻሻል የተደረገ ድጋፍ ክትትል (ከቅድመ 1 ኛ እስከ 2 ኛ ደረጃ)
- ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከክፍል (ውስጥና ውጭ) ግብአቶች ተሟልተው ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው፣
- ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ቅስቀሳ ስለመካሄዱ፣ የመሰረተ ልማት ግብዓቶች ተደራሽ ስለመሆናቸው፣
- የመማር ማስተማር ስራን ለማስጀመር የሚያስችል የተሟላ ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ስለመካሄዳቸው ስለመከታተል፣ አፈፃፀማቸውን ስለመቆጣጠር፣ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- ተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ሂደት እና የትምህርት ግብዓቶችን መሟላታቸውን ክትትል ስማድረግ ለመማር ማስተማር ዝግጁ መሆናቸውን ስለማረጋገጥ፣

ግብ **2**፡- ልዩ ፍላጎት ላላቸው እና ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ልዩ ድጋፍ በመስጠት ተሳትፏቸውን ማሻሻል

- የፆታ ንጽጽር ተሣትፎን ከቅድመ አንደኛ እስከ 2 ኛ ደረጃ እንዲሻሻል የተደረገ ክትትል፣
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች እና አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የሚማሩ ጐልማሶች ተሳትፎ እንዲሻሻል የተደረገ ክትትል፣
- ልዩ ፍላት ያላቸው ህፃናት የትምህርት ተሳትፎአቸው በፍትሃዊነት እንዲያድግ በየትምህርት ቤቱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች እንዲከናወኑ እና ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንዲቻል ለሚመለከው አካል ድጋፍ ስለማድረግ እና አፈጻጸሙን በመከታተል ግበረ መልስ ስለመስጠት፣
- የማታ ትምህርት በአፋን ኦሮሞ የሚሰጡ ተቋማት ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠታቸውን በክትትልና ድጋፍ ስለማረጋገጥ፣
- የ(ኦ) ክፍል ተማሪዎች ቅበላ አፋን ኦሮሞ ጨምሮ በፍትሃዊነት እንዲካሄድ ክትትል በማድረግ፣ ግብረመልስ ስለመስጠት፣

የትኩረት መስክ **2**፡- ጥራትና ተገቢነት ያለው መማር ማስተማር፡-

ግብ **3**፡- የትምህርት ጥራት ማሻሻል፡-

- በክፍለ ውስጥ ተከታታይ ምዘና በሳይንሳዊ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን በምልከታ ስለማረጋገጥ እና ክፍተቶች ላይ ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- መምህራን አሳታፊ የማስተማር ስነ ዘዴ በሳይንሳዊ መንገድ መጠቀማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ እና ክፍተቶች ላይ ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የተማሪዎች የውጤትና ስነ-ምግባር መሻሻል ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርመር በማካሄድ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- በክላስተር ሱፐርቪዥን ደረጃ የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድር በማድረግ በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ መፈጠሩን ስለማረጋገጥ፣
- የተከታታይ ምዘናና ፈተና ስራን በተገቢው ስታንዳርድ መሰረት እየሄደ መሆኑን በክትትልና ድጋፍ ስለማረጋገጥ፣
- በተማሪ ውጤትና ባህሪ ዙሪያ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በመገምገም ውጤታማ የሆኑት ለሌሎች እንዲዳረስ ስለማደረግ፣
- በተማሪ ውጤትና ባህርይ ማሳደግ ላይ የሚያተኩር የአንድ ገፅ ዕቅድ በማቀድ ወደ ተግባር ስለመግባት፣ አፈፃፃሙን በመከታተል ስለመገምገምና ግብረ-መልስ ስለመስጠት፣
- በትምህርት ሴክተሩ ስትራቴጂክና አመታዊ እቅድ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ቁልፍ ጉዳዮች ስለመለየት፣ የተለዩትን ስትራቴጂክና አመታዊ እቅድ ቁልፍ ጉዳዮች ለእቅድ ዝግጅት መነሻ እንዲሆኑ በየደረጃው ስለማሳወቅ፣ አፈፃፀሙን ስለመከታተል፣ ስለመገምገምና ግብረመልስ ስለመስጠት፣

- የክ/ከተማ፣ ወረዳና ትምህርት ቤት የተለያዩ ስትራቴጂክና መሪ እቅድ ዝግጅቶች ሂደቶችን ስለመከታተል፣ የተዘጋጁትን ስለመገምገም ሙያዊ ድጋፍ ስለመስጠት፣

- የትምህርት ቤት መሻሻል ስትራቴጂክ እቅድ በተሰጠው ስልጠና እና በአዲሱ መረጃ መሰብሰቢያ ስነዘዴና ግለ ግምገማ መሰረት ዕቅዱ በየደረጃው መዘጋጀቱን እና ቁልፍ ጉዳዮች መካተታቸውን የሱፐርቪዥን ሙያዊ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፤

- የመማር ማስተማሩን ሂደትና ውጤት ያሉባቸውን ክፍተቶች በመለየት ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣

- በትምህርት ቤቶች የአይሲቲ ቤተ-ሙከራና የኢንተርኔት አገልግሎት መጠናከሩን በክትትልና ድጋፍ ስለማረጋገጥ፣

- የትምህርት ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ሽፋን በመጀመሪያ ደረጃ እንዲሁም ከ 9ኛ-12ኛ፤ የስኩል ኔት አገልግሎት ሽፋን፤ የትምህርት በሬዲዮ ተደራሽነት እንዲሁም ፕላዝማ አግልግሎት ሽፋን እና ተደራሽነታቸውን ክትትል እና ድጋፍ ስለማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፣

- ለሁሉም የመንግስት ት/ቤቶች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያ ግብዓቶችን ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረገ (የመጽሀፍት፣ የዩኒፎርም፣ ደብተር ጫማ፣ጋወን፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ ማሸለቢያ ግብዓቶች፣ የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የሚያገለግሉ የህጻናት መጫወቻ፣ ...ወዘተ) እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግብዓቶችን (የመማሪያ ክፍሎች፤ የመመገቢያ እና ማብሰያ ቦታዎች፣ መጸዳጃ ቤት እና ሌሎች ግንባታዎች፤ የንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ ወዘተ...) አቅርቦትን እና ስርጭት ፍትሀዊነትን አፈጻጸሙን ክትትል እና ድጋፍ ስለማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፣
- ከባለድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር በመተባበር ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚመጡ የአካል ድጋፍ መሳሪያዎችና ሌሎች ተገቢነት ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ፍትሀዊ ስርጭት እና አፈጻጸሙን በመከታተል ግበረ መልስ ስለመስጠት፤
- የትምህርት መሣሪያዎች ለተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች ባግባቡ መድረሱንና ሥራ ላይ መዋሉን ስለመከታተል፣
- በልዩ ፍላጎት እየተሰሩ ያሉ መፀዳጃ ቤቶች እና ንፁህ የመጠጥ ውሀ ግንባታ ላይ ክትትል ስለማድረግ፣

ግብ **4፡-** የመማር ማስተማር ሂደትን መሻሻል

- መምህራን ተገቢውን የማስተማር ስነዘዴ በመምረጥ የመማር ማስተማር ስራ ማከናወናቸውን ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣
- የስርዓተ ትምህርት አተገባበርን በክፍል ምልከታ ስለማረጋገጥ፣
- መምህራን በየትምህርት ክፍላቸው የዓመት፣ የሴሚስተር፣ የወር፣ የሳምንት እና የእለት የትምህርት እቅድ ዝግጅታቸውን አጣጥመው መስራታቸውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ውጤታማነትን ዳሰሳ ጥናት በመስራት ስለመገምገም፣
- የተማሪዎች፣ የመምህራን፣ የወላጅችና የትምህርት አመራር (የአራትዮሽ) ስምምነት ተግባራዊነት ስለማረጋገጥ፣
- መምህራን በሳምንት የተሰጣቸውን ክፍለ ጊዜ ያለብክነት ማስተማራቸውን ክትትል በማድረግ ስለማረጋገጥ፣
- የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ስነ ዘዴና የክፍል አያያዝና አጠባበቅ ለመምህራን ስልጠና ስለመስጠት፣
- መምህራን በሳምንት የተሰጣቸውን ክፍለ ጊዜ ያለብክነት በማስተማር የዓመቱን ፖርሽን በአግባቡ ማጠናቀቃቸውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፣
- ለር/መምህራን፣ ለወረዳ እና ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች አስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን በማካሄድ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- መማር ማስተማሩን የሚያሻሽል ልምድ ልውውጥ ስለማካሄድ፣
- መማር ማስተማሩን የሚያሻሽል ተሞክዎችን ስለመቀመርና ስለማስፋት፣
- መምህራንና ትምህርት አመራሩ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለመፈተን የተመዘገቡትን በመለየት ግንዛቤ በመስጠት፤ በተግባራዊነቱ ዙሪያ ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣
- በመምህራንና በትምህርት አመራሮች የመማር ማስተማሩን ውጤታማነት ለማሻሻል የተሰሩ ጥናትና ምርምሮችን ለትምህርት ማህበረሰቡ እንዲቀርቡ በማድረግ ማስገምገምና ውጤታማ የሆኑት ለሌሎች እንዲሰፋ ስለማድረግ፣
- የመምህራንና ትምህርት አመራሩ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ተግባራትን በተገቢው ስታንዳርድ መሰረት መከናወኑን በመገምገም ግብረመልስ ስለመስጠት፣

- የሚዘጋጁ ፈተናዎችን ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር ማስተሳሰርና ተግባር ላይ መዋሉን በማረጋገጥ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የፈተናና ምዘና ዝግጅትና አስተዳደር በየትምህርት ቤቱ ጥራትና ተገቢነት ያለው እንዲሆን በየሩብ አመቱ የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ፣
- ሞዴል ፈተናዎች በየደረጃው መስጠቱን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፣
- ደረጃውን የጠበቀ ምዘና በየክፍል ደረጃው እና በየትምህርት አይነቱ እየተከናወነ መሆኑን ስለማረጋገጥ፣
- በወረዳ እና ክ/ከተማ ደረጃ በሚዘጋጁ ሞዴል ፈተናዎች ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ተግባራዊነታቸውን በመከታተል ግብረ መልስ ስለመስጠት፣
- በየትምህርት ቤቱ የሚዘጋጁ የፈተናና ምዘና ዝግጅትና አስተዳደር ስራዎች ጥራትና ተገቢነት ያላቸው እንዲሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ፤
- ሁሉም ክላስተሮች እና ሱፐርቫይዘሮች የተሟላ ሱፐርቫይዘር ስራ ላይ ስለመሆኑ፣
- የተጓደሉ ሱፐርቫይዘሮችና ክላስተሮች በስታንዳርዱ መሰረት እንዲሟሉ ክትትል ማድረግና ለሚመለከተው ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- እያንዳንዱ ክላስተር ማእከል በተሰጠው የክ/ጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ክሊኒካል ሱፐርቪዥን እያካሄደ ስለመሆኑ በ 9 ወሩ የተካሄደ ክፍለጊዜ ብዛት በቅድመ 1 ኛ እና 1 ኛደረጃ------------------በ 2 ኛ ደረጃ----------------- አናሊሲስ ስለመሰራቱ
- የክሊኒካል ሱፐርቪዥን ውጤታማነት ዳሰሳ ጥናት በ 117 ክላስተር እንዲካሄድ በማድረግ እንደ ከተማ የተጠቃለለ 1 የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣
- እያንዳንዱ ሱፐርቫይዘር የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ተግባራትን የ 60 ሰአት ጥናት በማከናወን፣ ፖርቲፎሊዮ መዘጋጀቱን ስለማረጋገጥ፣
- የሱፐርቪዥን አገልግሎት እርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በሚታዩ ክፍተቶች ዙሪያ የማስተካከያ ተግባራትን ስለማከናወን፣
- ለት/ት ቤት ለወረዳ እና ለክ/ከተማ ተቋማት የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገም በማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፤
- የሱፐርቪዥን አሰጣጥን ውጤታማነት የሚያሳይ ዳሰሳ ጥናት በየደረጃው ስለማካሄድ፣
- በሁሉም ትምህርት ቤቶች ሁሉም መምህራን፣ ር/መምህራን እና አንጋፋ መምህራን የርስ በርስ የውስጥ ሱፐርቪዥን እንዲያካሂዱ አቅጣጫ በማስቀመጥ የአፈፃፀም ሂደቱን በመምራት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- በውስጥ ሱፐርቪዥን ሂደት ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ተግባራትን በተገቢው ስታንዳርድ መሰረት መከናወኑን ስለመገምገም፣
- የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል የሚያግዙ ጥናትና ምርምሮች ስለመሰራታቸው፣
- የመማር ማስተማሩን ውጤታማነት ለማሻሻል በሱፐርቫይዘሮች የተሰሩ ጥናትና ምርምሮችን ለትምህርት ማህበረሰቡ እንዲቀርቡ መድረክ ስለማዘጋጀት፣ ውጤታማ የሆኑትን ለሌሎች እንዲሰፋ ስለማድረግ፣
- የተሰሩት ጥናትና ምርምሮች በመማር ማስተማሩ ላይ ተግባራዊ እንዲደረጉ ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣

ግብ **5፡-** ተገቢነት ያለው የስርአተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራን ማሻሻል

- ስርዓተ ትምህርቱ በተዘጋጀው ዓመታዊ የትምህርት ካላንደር መሰረት እየተተገበረ መሆኑን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ስለመስጠት፣
- የመጻህፍት ግምገማ በተገቢው ወቅት እንዲካሄድና ውጤታማ እንዲሆን ክትትል ስለማድረግ፣
- የተጓዳኝ ክበባትን አደረጃጀትና አሰራር ውጤታማነቱን ክትትል በማድረግ አፈፃፀሙን ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- ተማሪዎችና መምህራን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራ ላይ ያተኮረ መማር ማስተማር እንዲከተሉ አሰራሮችን በማዘጋጀት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ አፈፃፀሙንም ገምግሞ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት በፕላዝማ እና ስኩልኔት የተደገፈ መሆኑን ተከታትሎ ችግሮችን ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የ 1 ኛ ደረጃ ትምህርት የሬዲዮ ትምህርት አሰጣጥ ሂደትን አግባብነትና ውጤታማነት ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣

የትኩረት መስክ **3፡-** የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ማሳደግ፣

ግብ **6፡-** የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ማጎልበት፤

- የትምህርት ብክነትን ለመቀነስ በተማሪዎች ማርፈድ፣ ከክፍል መቅረት እና ትምህርት ማቋረጥ፣ ዙሪያ ክትትሎችን ስለማድረግና ዳሰሳ ጥናት በመስራት የሚያረፍዱበትን፣ ክፍል የሚቀሩበትንና ትምህርት የሚያቋርጡበትን ምክንያት በመለየት ትምህርት ቤቶች እንደ ነባራዊ ሁኔታቸው ችግሩን የሚፈቱበትን መንገድ ስለማሳየት፣ አፈፃፀሙን ስለመከታተል፣ ውጤታማነቱንም ስለማረጋገጥ፣
- ትምህርት ማቋረጥንና ክፍል መድገምን ለመቀነስ መምህራንና ር/መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ፍጥነት ደረጃ በየትምህርት አይነቱ በመለየት (ፈጣን "A"፣ መካከለኛ "B" እና ዝቅተኛ "C") ብዛታቸውን በማወቅ መካከለኛ እና ዝቅተኞችን ወደ ፈጣኑ ለማድረስ የማብቃት ስራ እንዲሰሩ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ስለማድረግ፣ አፈፃፀሙን ግብረመልስ በመስጠት ስለማስተካከል፣
- ክፍል መድገምን ለመቀነስ እና ውጤታማነትን ለማሳደግ መምህራን የትምህርት ይዘቱን በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስነዘዴ በመጠቀም እንዲያስተምሩ በክሊኒካል ሱፐርቪዥን ድጋፍ መስጠት፣ አፈፃፀሙንም ግምገማ በማካሄድ ግብረመልስ ስለማቅረብ፣
- በየትምህርት ተቋማቱ የሚገኙትን የ 2 ኛ ደረጃ ተማሪዎች የስነልቦና እና ምክር ባለሙያዎችን፣ በመጀመሪያ ደረጃ ያሉ የልዩ ፍላጎት ባለሙያዎችን አሰራር በመከታተል የሚታዩ ችግሮችን ግብረመልስ በመስጠት ስለማስተካከል፣
- በተማሪዎች ስነምግባር እና ስነልቦና ዙሪያ ዳሰሳ በማድረግ ከሚፈለገው ስነልቦናና ስነ-ምግባር አኳያ ያለውን ልዩነት የሚሸፍን የሙያዊ ድጋፍ ሰነድ (ማንዋል) በማዘጋጀት ለምክር ስለማቅረብና ለባለሙያዎች ግንዛቤ ስለመፍጠር፣
- የተማሪዎች የመዝለቅና የማጠናቀቅ ምጣኔ እንዲያድግ በሃገር አቀፍ እና ከተማ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶችን ስለማቅረብ በጥናቱ የተጠቆሙ መፍትሄዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ሙያዊ ሰነድ አዘጋጅቶ እንዲተገበር ስለማድረግ አፈፃፀሙንም በመከታተል ግብረመልስ ስለመስጠት፣

- የውስጥና የውጪ ተገልጋዮችን ቅሬታ የማቅረብ እና የመደመጥ መብትን ባከበረ መልኩ አገልግሎቶች እንዲከናወኑ በትምህርት ቤት፣ በወረዳ እና በክ/ከተማ ደረጃ ስለ አሰራሩ ሙያዊ ድጋፍ ስለመስጠትና አፈፃፀሙንም ግብረመልስ ስለመስጠት፣ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንም ስለመፍታት፣
- የሱፐርቪዥን ክላስተር ማእከላትን የውጤታማነት ማረጋገጫ ዳሰሳ ስለመካሄዱ፣
- የውጤት ተኮር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ አውቶሜሽን ሪፖርት ስለማዘጋጀት፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎትን ሽፋንና ጥራት ባግባቡ በየክላስተር ደረጃ በመስጠት በቅድመ 1ኛ እና 1ኛ ደረጃ ትምህርት እና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት የሱፐርቪዥን ክላስተር ማእከላት የተገልጋይ እርካታን ስለመለካትና በመተንተን በሚታዩ ችግሮች ዙሪያ የማስተካከያ ተግባራትን ስለማከናወን፣
- በዜጎች ስምምነት ቻርተር የተቀመጡ አገልግሎቶችን ተግባራዊነት በመከታተል አፈፃፀሙን ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የውስጥና የውጪ የመልካም አስተዳደር ስራዎችን አሰራር ለሁሉም ተገልጋይ ከአድሎ የፀዳ፣ ፍትሀዊና ግልጽ አሰራርን የተከተለ እንዲሆን ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የትምህርት የውስጥና የውጪ አዋኪ ጉዳዮችን ክትትል በማድረግና በመለየት የሚፈቱበትንም አቅጣጫ በማስቀመጥ ለሚመለከተው ግብረመልስ ስለማቅረብ፣ አፈፃፀሙንም ስለመከታተል፣
- ለሌብነትና ብልሹ አሰራር የሚያገልጡ ምንጮችን በመለየትና የማክሰሚያ ስልት በመቀየስ ወደ ተግባር እንዲገባ ስለማድረግና አፈፃፀሙን በመከታተል ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የመንግስት ሀብት ለመንግስት ሥራ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ስለማድረግ፤
- የክላስተሩን አጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን አጠቃላይ መረጃ ስለማደራጀትና ለሚመለከተው አካል ስለማቅረብ፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥንን የመረጃ ልውውጥ ተግባራት በቴክኖሎጂ የተደገፈና ፈጣን እንዲሆን ስለማድረግ፣
- የክላስተሩን አጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን አጠቃላይ መረጃ በኮሚኒኬሽን በኩል ለህዝብ ተደራሽ ስለማድረግ፣

ግብ **8፡-** ውጤታማ የሃብት አጠቃቀምን መሻሻል፣

- ደንብና መመሪያን የተከተለ የንብረትና የሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ፣ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- የግዥ ፍላጎቶችን በመለየት ለሚመለከተው ስለማቅረብ፤
- በየሱፐርቪዥን ክላስተር ማእከላት ያለውን የሰዉ ሃይል ፍላጎትን በመለየት በምደባ፣ በቅጥር፣ በደረጃ እድገትና በዝውውር እንዲሟላ ለሚመለከተው ጥያቄ ስለማቅረብ፣

ግብ **9፡-** የትምህርት ልማት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አፈፃፀም ማሳደግ፣

- በስርዓተ ትምህርቱ የተካተቱት የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ የትምህርት ይዘቶች በተግባር ተደግፈው ተግባራዊ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣
- የኤች አይ ቪና ፀረ-ድራግ ክበባት ተጠናክረው ስራቸውን እንዲያከናውኑ ክትትል እና ድጋፍ ስለማድረግ፣

- በሁሉም ትምህርት ቤቶች የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣
- በተማሪዎች ጤና ዙሪያ የሚታዩ የግንዛቤና ትግበራ ክፍተቶችን በክትትል በመለየት ግብረመልሶችን ስለመስጠት፣
- በተማሪዎች ምገባ ዙሪያ የሚታዩ የግንዛቤ እና ትግበራ ክፍተቶችን በመለየት የድጋፍ ክትትል ግብረመልስ ስራዎችን ስለመስራት፣
- በተማሪዎች የመማር ውጤትና ስነምግባር ላይ ወላጆች ሚናቸውን እንዲወጡ ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠትና ስራውን ስለማጠናከር፣
- ወላጁንና ህብረተሰቡን ከትምህርት ቤት ጋር በማቀራረብ የትምህርት ተቋማት ለመማር ምቹና ሰላማዊ እንዲሆኑ ወላጆችና ህብረተሰቡን ያሳተፈ ውይይት በየትምህርት ቤቱ እንዲኖር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠትና ስለማጠናከር፣
- የስርአተ ፆታ ጉዳዮችን በትምህርት ቤት ደረጃ ሜይንስትሪም ተደርገው ተማሪዎች ላይ መተግበራቸውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ ስለመስጠት፣

ግብ **10፡-** የመምህራን፤ የትምህርት አመራሩንና ባለሙያዎችን የመፈፀም አቅም ማሳደግ፣

- የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ፣ አጀመ እና ማህደረ ተግባር ስራዎችን ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣ በክፍተቱ ዙሪያ ስልጠና ስለመስጠት፣
- የክላስተሩ ሱፐርቫይዘሮችን የሙያ ክፍተት ዳሰሳ ጥናት ውጤትን መሰረት ያደገ አጫጭር ስልጠናዎችን ስለማዘጋጀትና ስለማሰልጠን፣
- ለር/መምህራንና ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች አስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን ድጋፍ ክትትል በማካሄድ ግብረ-መልስ ስለመስጠት፣ በክፍተቱ ዙሪያ ስልጠና ስለመስጠት፣
- መምህራንና ትምህርት አመራሩ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለመፈተን የተመዘገቡትን በመለየት ግንዛቤ ስለመስጠት፤ በተግባራዊነቱ ዙሪያ ክትትልና ድጋፍ ስለማድረግ፣